Mizan-Tepi University
Office of the President

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት

ቁጥር ሚቴዩ/18/883/59/11
Ref No.
ቀን
Date 0 3 ታህሳስ 2011

ለአካ/ጉዳ/ም/ፕ/ጽ/ቤት
ለአስ/ተማ/አገ/ም/ፕ/ጽ/ቤት
ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

ጉዳዩ:- መመሪያ መላክን ይመለከታል

በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዲስ መመሪያ ህዳር 13/2011 የፀደቀ መሆኑን የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በቀን 14/03/2011 በቁጥር 7/m259/674/11 በላከልን ደብዳቤ ያሳወቀን ስለሆነ ከፀደቀበት ዕለት ጀምሮ በመመሪያው መሰረት ወደ ስራ እንዲገባ አሳስባለው::

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:

- ለፕሬዝደንት ጽ/ቤት
- ለቴፒ ግቢ ዋና ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለቲቺንግ ሆስፒታል ዋና ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሰው ሀብትና ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርት ጥራትና አግባብነት ዳይሬክቶሬት
- ለህዝብና ውጪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

✉260 ☎047-135-2005/97 Fax 047-135-1771 መልስ ሲጽፉልን የእኛን ቁጥር ይጥቀሱ In replying, please quote our ref. no ሚዛን ተፈሪ / Mizan-Teferi

Ministry of ... and Higher Education

15/3/2011

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ለሐረማያ ዩኒቨርስቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርስቲ
ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርስቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ
ለሰመራ ዩኒቨርስቲ
ለአክሱም ዩኒቨርስቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ
ለዲላ ዩኒቨርስቲ
ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርስቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ
ለወለጋ ዩኒቨርስቲ
ለወሎ ዩኒቨርስቲ
ለደብረ ብርሃን ዩንቨርስቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርስቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ
ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ
ለባህርዳር ዩኒቨርስቲ
ለጎንደር ዩኒቨርስቲ
ለጅማ ዩኒቨርስቲ
ለጅግጂጋ ዩኒቨርስቲ
ለዋቻሞ ዩኒቨርስቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርስቲ
ለመቱ ዩኒቨርስቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ
ለወልድያ ዩኒቨርስቲ
ለራያ ዩኒቨርስቲ
ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ
ለመቅደላ አምባዩኒቨርስቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ
ለደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ
ለወራቤ ዩኒቨርስቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርስቲ
ለጂንካ ዩኒቨርስቲ
ለቀብሪ ደሃር ዩኒቨርስቲ
ለኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርስቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- መመሪያ መላክን ይመለከታል

በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ህዳር 13/2011 የፀደቀ መሆኑን እየገለፅን ከፀደቀበት ዕለት ጀምሮ ወደ ስራ እንዲገባ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሂሩት ወ/ማርያም ተከተል (ዶ/ር)
ሚኒስትር

*ግልባጭ*

- ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
  <u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

www.moshe.gov.et info@ethernet.edu.et www.facebook.com/SHE...
☎ +251 11 155 31 33 ፋክስ/FAX: - +251 11 1570686

# በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ

*መመሪያ ቁጥር 01/2011*

[ሕዳር 11/2011ዓ.ም

በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ

ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን የሚጠበቅባቸውን ብቁ የሰው ኃይል ያፈሩ ዘንድ፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮች እንዲያከናወኑ እንደዚሁም ውጤታማ የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ማከናወን እንዲችሉ የመምህራኑ ሚና አስተዋጽኦ ከወሳኝ በላይ በመሆኑ ፤

መምህራን በአገራችን ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የበለፀገ ኢኮኖሚና ማህበረሰብ በመፍጠር ስራ ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ መወጣት ስለሚጠበቅባቸው ፤

መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በአካዳሚያዊ ቤተሰባዊነት መልኩ መቃኘት ያለበት በመሆኑና መምህራን ለተማሪዎቻቸው፣ ለአጠቃላይ የትምህርት ማህበረሰብና መላው ህዝብ በሚሰጡት ፍቅር፣ ለአገር ባላቸው ተቆርቋሪነትና ለስራ በሚሰጡት ክብር መልካም ተምሳሌትና አርአያ መሆን ስለሚጠበቅባቸው፤

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉባቸው አካባቢዎች በከፍተኛ ትምህርት ትሩፋት እንዲለወጡ በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ መምህራን የማህበረሰቡን እሴቶች በማክበርና በፍፁም ጨዋነት አብረው መሥራት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ

የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በሚያስቀምጠው መሰረት ተቋማት የሰው ኃይላቸውን እንዲቀጥሩ ፤ እንደሚያለሙና በውጤታማነት ላይ ተመስርተው እንዲያበረታቱ /እንዲያቀዩ ወይም እንዲያሰናብቱ ለማስቻል አገራዊ የሆነ ወጥ መመሪያ በማስፈለጉ

ተቋማት መምህራኑንም ሆነ ሌሎች የተቋሙን ሰራተኞች ለመቅጠር፣ ለማስተዳደርና ለማልማት በአዋጅ የተሰጣቸው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አገር አነስተኛውን የመምረጫ መስፈርትና ተቋማት መከተል ያለባቸውን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ይህ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ ፡ አጠቃላይ ጉዳዮች

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ምልመላ ፡ ቅጥርና ልማት መመሪያ ቁጥር 01/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. አውጪው አካል

   ~~የሳይንስና~~ ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በአስፈፃሚ አካላ~~ትና~~ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በተሰጠው ስልጣን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

   ይህ መመሪያ ተጠሪነታቸው ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በሆኑ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊያን መምህራንን በመልመል ፡ በመቅጠርና በማልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

4. የፆታ አገላለጽ

   በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው በሴት ሴትንም ያካትታል፡፡

5. አግባብነት ያላቸው ህጎች

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ያሉ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደርን የተመለከቱ አዋጆችና ደንቦች ጋር በሚጣጣም መልኩ የሚተገበር ይሆናል፡፡

6. የውስጥ መተዳደሪያ መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ መተግበር የሚያስችላቸው የውስጥ አሰራር መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡ ይህም ሆኖ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን አነስተኛ መስፈርቶችን መቀየር አይቻልም፡፡

## ክፍል ሁለት፡ የመምህራን አመላመል ስርዓት

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራኖቻቸውን አካዳሚያዊ ብቃትን ማዕከል በማድረግ ለማስተማርና ለምርምር ባላቸው ፍላጎትና ዝንባሌ እንደዚሁም ተማሪዎች የተስተካከለ ስብዕና እንዲኖራቸው ዓርአያ መሆን የሚችሉትን ከቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው፣ ከሌሎች ተቋማት የድህረ ምረቃ ት/ቤቶች ምሩቃን ፣ ከኢንዱስትሪውና ከምርምር ተቋማት ይመለምላሉ፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከራሳቸውና ከሌሎች ተቋማት የሚመለምሉና የሚቀጠሯቸው መምህራን ብዛት አካዳሚያዊ ባህል ብዝሃነት ማሳደግ በሚያስችል አግባብ ምጥጥኑን ጠብቀው መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሲፈፀም በተቋሙ በተማሩትና በሌሎች ተቋማት ተምረው የሚቀጠሩት መካከል ሚዛኑን የጠበቀ ምጥጥን እንዲኖር ማድረግ ከኢንዱስትሪ (ከሥራ ዓለም) እና/ወይም ምርምር ተቋማት የሚመለምሉ እጩዎች ቢያንስ ቀጥር ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ እንደሆነ ባስተማሩባቸው አመታት የነበራቸውን የስራ አፈጻፀም ውጤት መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ተቋማት ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎቻቸው ተቢ መምህራንን መመልመል ሲያስፈልጋቸው የሚመለምሏቸው እጩ መምህራን ከአካዳሚያዊ አፈፃፀማቸው ባሻገር ኃላፊነት ለመውሰድ ፣ ሌሎችን ለማስተባበርና ለመምራት እንደዚሁም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት የነበራቸው ተሳትፎና እንቅስቃሴ ከግንዛቤ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሲፈፀም በትምህርት ክፍል ካውንስል ዝርዝር ግምገማ ተደርጎ እነኚህ ተመልማዮች በአሳማኝ መስፈርት መለየታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አግባብ የሚመለመሉት መምህራን ብዛት በአንድ ዓመት በአንድ ትምህርት ክፍል የሚመለመሉት ከሁለት መብለጥ የለበትም ፡፡

ተቋማት ከድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው (የሌላ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ባልደረባ ያልሆነ ብቻ ይመለከታል) እጩ መምህራን ሲመለመሉ የላቀ አካዳሚያዊ አፈፃፀም፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታና መልካም ስነ ምግባር ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በጥናትና-ምርምር ያሳዩት አፈፃፀም፣ የመመርቂያ ጥናትና ምርምር ስራቸው ተግቢነትና ችግር ፈቺነት በልዩ ጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት፡ የመምህራን አቀጣጠር ስርዓት

### 3.1. አጠቃላይ መርሆዎች

ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቅጥርን በተመለከተ ከቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው መልምለው ከሚያስቀሯቸው /ከሚቀጥሯቸው በስተቀር አገራዊ ተደራሽነትና ሽፋን ባለው(ጋዜጣ፡ ቴሌቪዥን) በግልጽ ማስታወቂያ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የስራ ማስታወቂያው በተቋማቱ ድረ ገፅ ላይና ሌሎች የተቋማቱ መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ማስታወቂያው የሚወጣበት ወቅትና ለአመልካቾች የሚሰጠው የማመልከቻ ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የማስመረቂያ ጊዜ ፡ የማመልከቻ ቦታና የማመልከቻ ማቅረቢያ አማራጮችን ፡ የስራ የማስታወቂያው መረጃ ለሌሎች በቀላሉ ሊደርስ የሚችልበትን ሁኔታ ፡ የተቋማትን አካዳሚክ ካለንደርና ሌሎች ጉዳዬችን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ተቋማቱ በአንድ ቅጥር ማስታወቂያ የሚፈለገው ያህል ተወዳዳሪ አመልካቾች አልቀረቡም ብለው ሲያምኑ ድጋሚ ማስታወቂያ ሊያወጡ ይችላሉ፡ ይህም ሲፈፀም በመጀመሪያው ማስታወቂያ ያመለከቱት አመልካቾች ማስታወቂያው በድጋሚ እየወጣ ስለመሆኑ በአድራሻቸው መረጃ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

ለአንድ ክፍት መደብ በቂ አመልካቾች አልቀረቡም ተብሎ የሚነገረው ከአስር በታች አመልካቾች ያመለከቱ እንደሆነ ነው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በአንዳንድ መስኮች ተቋማት ተደጋጋሚ ማስታወቂያ( ቢያንስ ሁለት) አውጥተው በቂ አመልካቾች የማይገኙ ከሆነ ከአስር በታች አመልካቾች ቢቀርቡም ቅጥር ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

### 3.2. መለያ መስፈርቶችና ዋጋቸው

እድሜ

በረዳት ምሩቅነት ለሚቀጠሩ የመጀመሪያ ድግሪ ምሩቃን በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሚያቸው ከሰላሳ አምስት (35) አመት መብለጥ የለበትም፡፡

በሌክቸረርነት ለሚቀጠሩ በሁለተኛ ድግሪ ለተመረቁ ወይም ከስራ አለም ለሚቀጠሩ በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሚያቸው ከአርባ አምስት (45)ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

#### 3.2.1. አካዳሚክ አፈፃፀም የተጠቃለለ ውጤት (Cumulative GPA)

<u>በረዳት ምሩቅነት ለመቀጠር</u>

ለወንዶች፡ 3.25ና ከዚያ በላይ

ለሴቶች ፡3.00ና ከዚያ በላይ

ለአካል ጉዳተኞች፡ 2.75ና ከዚያ በላይ

ለታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር አከባቢ ነባር ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች፡ 2.75ና ከዚያ በላይ

ከአንድ በላይ የበጎ ልዩነት( Affirmative Action ) ተጠቃሚዎች፡ 2.50ና

ለሁሉም የህክምና ድግሪ (የሰውና የእንስሳ) 3.00 ከዚያ በላይ ሆኖ በሚታወቅ የጤና እክል በተከሰተ የፈተና አለመውሰድ ችግር ሊፈቀድ ከሚችል ቢበዛ ሁለት Fx ውጭ ማስተናገድ

አይቻልም፡፡ ረዳት ምሩቃን የሚቀጠሩት ከዛው ተቋም ብቻ ስለሆነ ትምህርት ክፍሎች የተደራጀ መረጃ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

**በሌክቸረርነት ለመቀጠር**

ለወንዶች፡ 3.50ና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 3.00ና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ለሴቶች ፡3.35ና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.75ና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ለአካል ጉዳተኞች፡ 3.15 ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.50ና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ለታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር አከባቢ ነባር ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች፡ 3.15ና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.50ና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ከአንድ በላይ የበጎ ልዩነት(Affirmative Action ) ተጠቃሚዎች፡ 3.10ና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.50ና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ሆኖ በቆይታቸው Probation ገብቶ የማያውቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

በሌክቸረርነት የሚቀጠሩ ሁሉም (በመጀመርያ ድግሪያቸው በሌክቸረርነት የሚቀጠሩትን የህክምና ዶክተሮች ሳይጨምር) ቢያንስ ሁለት ዓመት ቆይታ ያለው ድህረ ምረቃ ትምህርት የተከታተሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመመረቂያ ፅሑፋቸው፡ B+, Very Good ወይም ተመጣጣኝ ያስመዘገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ተወዳዳሪዎች በሌላ የውጤት አያያዝ የተማሩ እንደሆነ ተመጣጣኙን በማስላት የሚያዝላቸው ይሆናል፡፡

በውጭ አገራት ትምህርታቸውን የተከታተሉ ተወዳዳሪዎች በሀገ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት የትምህርት ደረጃ አቻ ግመታና ሰነድ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአካዳሚክ ውጤት አፈፃፀማቸውን ለመለየት የተቀመጠው አነስተኛው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ላሉ ክፍት ቦታዎች ያመለከቱት ተወዳዳሪዎች ቁጥር በዛ ያለ ሆኖ ሲያገኙት ተቋማት ከፍ ያለ የመቁረጫ ነጥብ ያመጡትን ብቻ ለቀጣይ ውድድር ሊለዩዋቸው ይችላሉ፡፡ በዛ ያሉ አመልካቾች ቀርበዋል ተብሎ የሚነገረው ለአንድ ክፍት መደብ ሃያ (20)ና ከዚያ በላይ አመልካቾች የቀረቡ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሲፈፀምም ለእያንዳንዱ ክፍት መደብ ቢያንስ 10 አመልካቾች ለመጨረሻ ማጣሪያ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

የፒኤችዲ(PhD) እና ከዚያ በላይ ያለ ቅጥር በተቋማት የውስጥ መመሪያ ይሸፈናል፡፡

3.2.2. አካዳሚክ እርከኖችና ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

**ሀ. ከመጀመሪያ ድግሪ ተመልምለው በረዳት ምሩቅነት ለሚቀጠሩ ስራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች**

- አካዳሚያዊ አፈፃፀም (35)
- የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክና የእንግሊዘኛ ቋንቋ የፅሁፍ ፈተና ውጤት (35)
- ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፡ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት(20)
- ከትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚሰጥ ምስክርነት(Recommendation) (10)

ለ. ከድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው መልምለው በሌክቸረርነት ለሚቀጠሩት ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

- አካዳሚያዊ አፈፃፀም (30)
- የፅሁፍ ፈተና ውጤት (30)
- ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት(10)
- የመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት(30)

ሐ. በሁለተኛ ድግሪ ተመርቀው ከሥራ ዓለም፣ ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሩቃን፣ ከምርምር ተቋማት ለሚቀጠሩት ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

- አካዳሚያዊ አፈፃፀም (30)
- የፅሁፍ ፈተና ውጤት (30)
- ምስለ ማስተማር (Demo)(10)
- ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት(10)
- የየመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት(20)

### 3.3. የመምህራን ቅጥር አፈፃፀም

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚቀጠር መምህር በተወሰነ ጊዜ/ዓመታት ሊታደስ በሚችል ውል መቀጠር አለበት፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አስር ዓመትና ከዚያ በላይ ያስተማረ ወይም የተባባሪ ፕሮፌሰር ማዕረግ የደረሰ መምህር በቋሚነት ሊቀጠር ይችላል፡፡ በሌሎች ህጎች ተደንግገው በሰራተኛ ቅጥር መካተት ያለባቸው ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ውሉ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

- የስራ ዝርዝር የሚገልጽ፣
- መብትና ግዴታዎችን የሚያስቀምጥ፣
- በተከታታይ ግምገማና የጊዜ ገደብ ውል የሚታደስ ወይም የሚቋረጥ መሆኑን፣

## ክፍል አራት ፡ መምህራን ልማትን በተመለከተ

የመምህራን ቅጥር በቀጣይነት የመምህራኑን አቅም ከማሳደግና ከማልማት ጋር መተሳሰር ይኖርበታል፡፡ አዲስ ወደ ተቋሙ በቅጥር የሚቀላቀሉትም ይሁን በ~~ሥራ ላይ~~ የቆዩ ወይም ለቀጣይ ትምህርት ተልከው የሚመለሱት መሰልጠን ያለባቸውን ሥልጠና ርዕስ መለየት ይገባል፡፡

### 4.1 የረዳት ምሩቃን በተመለከተ የሚከናወኑ የመምህራን ልማት ሥራዎች

1. ረዳት ምሩቃን ምንም እንኳ የተቋሙ ተማሪዎች የነበሩ ቢሆንም ወደ ሥራው ዓለምና ወደ ሠራተኛነት ሲቀየሩ ቢያንስ በሚከተሉት ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፣

   - በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው
     በአገራዊ የከፍተኛ ትምህርት አቅጣጫዎችና የህግ ማዕቀፎች

- በተቋሙ የሴኔት ሌጂስሌሽንና ሌሎች የውስጥ አሰራር ደንቦች
- በተቋሙ የሠራተኞችና መምህራን ዲስፕሊንና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው መመሪያዎች
- በመምህራን ስነ ምግባር ኮድ
- ለሚማሩበት የሁለተኛ ድግሪ መስክ አስፈላጊ የሆነ ግን በቅድመ ምረቃ ትምህርት ያልተካተቱ የተጨማሪ ሥልጠናዎች እንደ አስፈላጊነቱ መውሰድ

2. ተቋማት ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጥቂቶችን መልምለው በረዳት ምሩቅ ደረጃ ሲቀጥሯቸው ዋናው ሥራቸው ኮርስ ማስተማር መሆን የለበትም፡፡ረዳት ምሩቃን ዋና መምህራንን በመርዳት፣የትምህርት ግብዓትና መርጃዎችን በማዘጋጀት፣ የፈተና ወረቀቶችን/አሳይመንቶችን በማረምና ቲቶርያሎችን በመስጠት ራሳቸውን ለድህረ ምረቃ እያዘጋጁ መቆየት ይኖርባቸዋል፡፡

3. ረዳት ምሩቃን ከተመረቁበት የመጀመሪያ ድግሪ ጥቅል ጉዳዮች ውስጥ ለአካዳሚክ ካሪየሩ የሚሆኗቸውን የትኩረት መስክ በመለየት በመስኩ የካበተ ልምድ ያላቸውን በማማከር ለቀጣዩ የድህረ ምረቃ ትምህርት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ረዳት ምሩቃን የሚሰለጥኑበት የድህረ ምረቃ መስክ የትምህርት ክፍሉን የመምህራን ሙያ ብዝሃነት፣ የተቋሙን መምህራን ልማትና የረዳት ምሩቃን የትኩረት መስክ ምርጫ ባማከለ መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 4.2 ሌክቸረሮችን በተመለከተ የሚከናወኑ መምህራን ልማት ሥራዎች

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከራሳቸው ረዳት ምሩቃን ለሁለተኛ ዲግሪ በመላክ ያስተማሯቸውን ይሁን ከውጭ የቀጠሯቸውን የመማር ማስተማሩን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ከላይ ለረዳት ምሩቃን እንዲሰጡ ከተለዩ የሥልጠና ርዕሶች በተጨማሪ

- የከፍተኛ ዲፕሎማ ሥልጠና
- የማስተማር ስነ ዘዴ ተጨማሪ ሥልጠናዎች
- የተቋሙን የምርምር ትኩረት መስኮችና ያሉ የምርምር/ጥናት እድሎች
- መረጃ ለመያዝ፣ለማደራጀትና ለመተንተን የሚያግዙ ሶፍትዌሮች ሥልጠና
- ሌሎች እንደ ሙያ መስኩ የሚጨመሩ ሥልጠና ርዕሶች

## 4.3. ቀጣይ ትምህርት እድሎችና ሥልጠና አፈፃፀም

መምህራን ከአንድ ትምህርት ደረጃ ከፍ ወዳለ የትምህርት ደረጃ ለስልጠና ሲላኩ ከቀጣሪ ተቋሙ ጋር ውል መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በመምህራኑና በተቋማት መካከል የሚታሰረው ውል ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተ~~ት ይኖ~~ርበታል፡፡

- የተፈቀደው የቆይታ እርዝማኔ( በዓመት)
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚሰጠው ድጋፍ(ድጎማ)(ካለ)
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ በሚቆይበት ወቅት የሚከፈለው ደሞዝ መጠን
- ቀጣሪው ተቋም ሰልጣኙ መምህር ትምህርቱን በስኬት አጠናቆ ሲመለስ በሚያሟላበት እርከን መልሶ እንደሚቀጥረው
- ሰልጣኙ መምህር ሥልጠና ላይ ለሚቆይባቸው ዓመታት እጥፍ ቀጣሪውን ለማገልገል መስማማቱን

- በተቋሙ የሴኔት ሊጂስሌሽንና ሌሎች የውስጥ አሰራር ደንቦች
- በተቋሙ የሠራተኞችና መምህራን ዲስፒሊንና ሌሎች ተግዜነት ያላቸው መመሪያዎች
- በመምህራን ስነ ምግባር ኮድ
- ለሚማሩበት የሁለተኛ ድግሪ መስክ አስፈላጊ የሆነ ግን በቅድመ ምረቃ ትምህርት ያልተካተቱ የተጨማሪ ሥልጠናዎች እንደ አስፈላጊነቱ መውሰድ

2. ተቋማት ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጥቂቶችን መልምለው በረዳት ምሩቅ ደረጃ ሲቀጥሯቸው ዋናው ሥራቸው ክርስ ማስተማር መሆን የለበትም።ረዳት ምሩቃን ዋና መምህራንን በመርዳት፣የትምህርት ግብዓትና መርጃዎችን በማዘጋጀት፣ የሬተና ወረቀቶችን/አሳይመንቶችን በማረምና ቱቶርያሎችን በመስጠት ራሳቸውን ለድህረ ምረቃ እያዘጋጁ መቆየት ይኖርባቸዋል።

3. ረዳት ምሩቃን ከተመረቁበት የመጀመሪያ ድግሪ ጥቅል ጉዳዮች ውስጥ ለአካዳሚክ ካሪየር የሚሆናቸውን የትኩረት መስክ በመለየት በመስኩ የካበተ ልምድ ያላቸውን በማማከር ለቀጣዩ የድህረ ምረቃ ትምህርት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ረዳት ምሩቃን የሚሰልጥኑበት የድህረ ምረቃ መስክ የትምህርት ክፍሉን የመምህራን ሙያ ብዝሃነት፣ የተቋሙን መምህራን ልማትና የረዳት ምሩቃን የትኩረት መስክ ምርጫ ባጣጣመ መልኩ መፈፀም ይኖርበታል።

## 4.2 ሌክቸረሮችን በተመለከተ የሚከናወኑ መምህራን ልማት ሥራዎች

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከራሳቸው ረዳት ምሩቃን ለሁለተኛ ዲግሪ በመላክ ያስተማሯቸውን ይሁን ከውጭ የቀጠሯቸውን የመማር ማስተማሩን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ከላይ ለረዳት ምሩቃን እንዲሰጡ ከተለዩ የሥልጠና ርዕሶች በተጨማሪ

- የከፍተኛ ዲፕሎማ ሥልጠና
- የማስተማር ስነ ዘዴ ተጨማሪ ሥልጠናዎች
- የተቋሙን የምርምር ትኩረት መስኮችና ያሉ የምርምር/ጥናት እድሎች
- መረጃ ለመያዝ፣ለማደራጀትና ለመተንተን የሚያግዙ ሶፍትዌሮች ሥልጠና
- ሌሎች እንደ ሙያ መስኩ የሚጨመሩ ሥልጠና ርዕሶች

## 4.3. ቀጣይ ትምህርት እድሎችና ሥልጠና አፈፃፀም

መምህራን ከአንድ ትምህርት ደረጃ ከፍ ወዳለ የትምህርት ደረጃ ለስልጠና ሲላኩ ከቀጣሪ ተቋሙ ጋር ውል መያዝ ይኖርባቸዋል። በመምህራኑና በተቋማት መካከል የሚታሰረው ውል ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

- የተፈቀደው የቆይታ እርዝማኔ( በዓመት)
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚሰጠው ድጋፍ(ድጎማ)(ካለ)
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ በሚቆይበት ወቅት የሚከፈለው ደሞዝ መጠን
- ቀጣሪው ተቋም ሰልጣኙ መምህር ትምህርቱን በስኬት አጠናቆ ሲመለስ በሚያሚላበት እርከን መልሶ እንደሚቀጥረው
- ሰልጣኙ መምህር ሥልጠና ላይ ለሚቆይባቸው ዓመታት እጥፍ ቀጣሪውን ለማገልገል መስማማቱን

- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚወጣበትን ጠቅላላ ወጪ( ደሞዝ፣ድጎማ ወይም ድጋፍ፣የምርምር ሥራ ድጋፍ፣ የትምህርት ወጪ ሌሎች በራሳቸው ከፍለው የሚማሩት ከሚከፍሉት የማይበልጥ፣ ወዘተ) በውል የሚቀመጥ ግዴታ መግባትና ለዚህም ዋስ ማቅረብ ያለበት መሆኑ
- ለትምህርት የተሰጠውን ፈቃድ (Study Leave) ለትምህርቱና ለትምህርቱ ብቻ ማዋል እንዳለበት

## ክፍል አምስት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 5.1. እኩል የመቀጠር መብትን በተመለከተ

ተቋማት ብቃት ያላቸውን መምህራን ለመቅጠር በተለያዩ መልኩና መመዘኛዎች ብቃታቸውን ከማረጋገጥ ባለፈ በሥልጠና አማራጮችና ሥልቶች መካከል ልዩነት /አድልዎ ማድረግ አይችሉም፡፡

### 5.2. የተሻሩና የተተኩ አሰራር ሥርዓቶችን በተመለከተ

ከአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊ መምህራን ቅጥርን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በትምህርት ሚኒስቴር የወጡ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 5.3. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን የማሻሻል ሥልጣን አለው፡፡

### 5.4. መመሪያው ሥራ ላይ ስለሚውልበት

መመርያው በሚኒስትሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

===================///===================

---------------------------------------------

ሂሩት ወ/ማሪያም(ዶ/ር)
የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር
ሕዳር13 - 2011

Mizan-Tepi University
Office of the President

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት

ቀን
Date
ቁጥር
Ref No

ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕ/ጽ/ቤት
ለአስተዳደርና ተማሪዎች አገ/ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
ለቴፒ-ግቢ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ለቲቺንግ ሆስፒታል ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ለሰው ሀብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

ጉዳዩ፡- የሀገር ውስጥ መምህራን ምልመላና ቅጥር መመሪያን ስለመላክ፣

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የትምህርት ሚኒስቴር በቁጥር 7/ጠ259/259/1 በቀን 8/12/2010 ከነሐሴ 07/2010 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የሀገር ውስጥ መምህራን ምልመላ ቅጥርና ልማት መመሪያ ልኳል፡፡ በዚህ መሠረት ለተግባራዊነት እንዲረዳ የተላከልን ባለ10 ገፅ መመሪያ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

- ለፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለተቋማዊ ለውጥ ዳይሬክቶሬት

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

☏ 047-135-2005/2097
Fax 047-135-1771

መልስ ሲጽፉልን የእኛን ቁጥር ይጥቀሱ
In replying, please quote our ref. no

✉ 260
Mizan Teferi ሚዛን ተፈሪ

# በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ

ትምህርት ሚኒስቴር
7/1/2010

# በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ

ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን የሚጠበቅባቸውን ብቁ የሰው ኃይል ያፈሩ ዘንድ፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮች እንዲያከናውኑ እንደዚሁም ውጤታማ የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ማከናወን እንዲችሉ የመምህራኑ ሚናና አስተዋጽኦ ከወሳኝ በላይ በመሆኑ ፤ መምህራን በአገራችን ማህበራዊ ፤ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የበለፀገ ኢኮኖሚና ማህበረሰብ በመፍጠር ስራ ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ መወጣት ስለሚጠበቅባቸው ፤

መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በአካዳሚያዊ ቤተሰባዊነት መልኩ መቃኘት ያለበት በመሆኑና መምህራን ለተማሪዎቻቸው፣ ለአጠቃላይ የትምህርት ማህበረሰብና መላው ህዝብ በሚሰጡት ፍቅር፣ ለአገር ባላቸው ተቆርቋሪነትና ለስራ በሚሰጡት ክብር መልካም ተምሳሌትና አርአያ መሆን ስለሚጠበቅባቸው፣

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉባቸው አካባቢዎች በከፍተኛ ትምህርት ትሩፋት እንዲለወጡ በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ መምህራን የማህበረሰቡን እሴቶች በማክበርና በፍፁም ጨዋነት አብረው መሥራት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ፤

የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በሚያስቀምጠው መሰረት ተቋማት የሰው ኃይላቸውን እንዲቀጥሩ ፤ እንደሚያለሙና በውጤታማነት ላይ ተመስርተው እንዲያበረታቱ /እንዲያቆዩ ወይም እንዲያሰናብቱ ለማስቻል አገራዊ የሆነ ወጥ መመሪያ በማስፈለጉ፤

ተቋማት መምህራንንም ሆነ ሌሎች የተቋሙን ሰራተኞች ለመቅጠር፣ ለማስተዳደርና ለማልማት በአዋጅ የተሰጣቸው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አገር አነስተኛውን የመምረጫ መስፈርትና ተቋማት መከተል ያለባቸውን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ይህ **በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት መመሪያ** ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ ፡ አጠቃላይ ጉዳዮች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ምልመላ ፤ ቅጥርና ልማት መመሪያ ቁጥር 03 /2010 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. አውጪው አካል**

ትምህርት ሚኒስቴር በአስፈፃሚ አካላትና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በተሰጠው ስልጣን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ተጠሪነታቸው ለትምህርት ሚኒስቴር በሆኑ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊያን መምህራንን በመልመል ፣ በመቅጠርና በማልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

4. የፆታ አገላለጽ

 በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው በሙሉ ሴትንም ያካትታል፡፡

5. አግባብነት ያላቸው ህጎች

 ይህ መመሪያ ፀንተው ያሉ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደርን የተመለከቱ አዋጆችና ደንቦች ጋር በሚጣጣም መልኩ የሚተገበር ይሆናል፡፡

6. የውስጥ መተዳደሪያ መመሪያ የማውጣት ስልጣን

 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ መተግበር የሚያስችላቸው የውስጥ አሰራር መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡ ይህም ሆኖ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን አነስተኛ መስፈርቶችን መቀየር አይቻልም፡፡

## ክፍል ሁለት፡ የመምህራን አመላመል ስርዓት

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራኖቻቸውን አካዳሚያዊ ብቃትን ማዕከል በማድረግ ለማስተማርና ለምርምር ባላቸው ፍላጐትና ዝንባሌ እንደዚሁም ተማሪዎች የተስተካከለ ስብዕና እንዲኖራቸው ዓርአያ መሆን የሚችሉትን ከቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው፣ ከሌሎች ተቋማት ድህረ ምረቃ ት/ቤቶች ምሩቃን ፣ ከኢንዱስትሪውና ከምርምር ተቋማት ይመለምላሉ፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከራሳቸውና ከሌሎች ተቋማት የሚመለምሉና የሚቀጠሯቸው መምህራን ብዛት አካዳሚያዊ ባህል ብዝሃነት ማሳደግ በሚያስችል አግባብ ምጥጥኑን ጠብቀው መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሲፈፀም በተቋሙ በተማሩትና በሌሎች ተቋማት ተምረው የሚቀጠሩት መካከል ሚዛኑን የጠበቀ ምጥጥን እንዲኖር ማድረግ ከኢንዱስትሪ (ከሥራ ዓለም) እና/ወይም ምርምር ተቋማት የሚመለምሉ እጩዎች ቢጋራ ቅጥር ታቅፈው ሲሰሩ የነበሩ እንደሆነ ባስተማሩባቸው አመታት የነበራቸውን የስራ አፈፃፀም ውጤት መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ተቋማት ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎቻቸው ተኪ መምህራንን መመልመል ቢያስፈልጋቸው የሚመለምሏቸው እጩ መምህራን ከአካዳሚያዊ አፈፃፀማቸው ባለፈ ኃላፊነት ለመውሰድ ፣ ሌሎችን ለማስተባበርና ለመምራት እንደዚሁም የበጐ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት የነበራቸው ተሳትፎና እንቅስቃሴ ከግንዛቤ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሲፈፀም በትምህርት ክፍሉ ካውንስል ዝርዝር ግምገማ ተደርጎ እነኚህ ተመልማዮች በአሳማኝ መስፈርት መለያታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አግባብ የሚመለመሉት መምህራን

ብዛት በአንድ ዓመት በአንድ ትምህርት ክፍል የሚመለመሉት ከሁለት መብለጥ የለበትም ፡፡

ተቋማት ከድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው (የሌላ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ባልደረባ ያልሆነ ብቻ ይመለከታል) እጩ መምህራን ሲመለመሉ የላቀ አካዳሚያዊ አፈፃፀም፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታና መልካም ስነ ምግባር ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በጥናትና ምርምር ያሳዩት አፈፃፀም፣ የመመረቂያ ጥናትና ምርምር ስራቸው ተገቢነትና ችግር ፈቺነት በልዩ ጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሶስት፡ የመምህራን አቀጣጠር ስርዓት

## 3.1. አጠቃላይ መርሆዎች

ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቅጥርን በተመለከተ ከቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው መልምለው ከሚያስቀሯቸው /ከሚቀጥሯቸው በስተቀር አገራዊ ተደራሽነትና ሽፋን ባለው(ጋዜጣ፣ ቴሌቪዥን) በግልጽ ማስታወቂያ የሚፈፀም ይሆናል:: በተጨማሪም የስራ ማስታወቂያው በተቋሚቱ ድረ ገፅ ላይና ሌሎች የተቋሚቱ መረጃ ማሰራጫ መንገዶች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል::

ማስታወቂያው የሚወጣበት ወቅትና ለአመልካቾች የሚሰጠው የማመልከቻ ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የማስመረቂያ ጊዜ ፣ የማመልከቻ ቦታና የማመልከቻ ማቅረቢያ አማራጮችን ፣ የስራ የማስታወቂያው መረጃ ለሌሎች በቀላሉ ሊደርስ የሚችልበትን ሁኔታ ፣ የተቋማትን አካዳሚክ ካለንደርና ሌሎች ጉዳዩችን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል::

ተቋማቱ በአንድ ቅጥር ማስታወቂያ የሚፈለገው ያህል ተወዳዳሪ አመልካቾች አልቀረቡም ብለው ሲያምኑ ድጋሚ ማስታወቂያ ሊያወጡ ይችላሉ፤ ይህም ሲፈፀም በመጀመሪያው ማስታወቂያ ያመለከቱት አመለካቾች ማስታወቂያው በድጋሚ እየወጣ ስለመሆኑ በአድራሻቸው መረጃ ሊደርሳቸው ይገባል::

ለአንድ ክፍት መደብ በቂ አመልካቾች አልቀረቡም ተብሎ የሚነገረው ከአስር በታች አመልካቾች ያመለከቱ እንደሆነ ነው::

ይህ እንዳለ ሆኖ በአንዳንድ መስኮች ተቋማት ተደጋጋሚ ማስታወቂያ( ቢያንስ ሁለት) አውጥተው በቂ አመልካቾች የማይገኙ ከሆነ ከአስር በታች አመልካቾች ቢቀርቡም ቅጥር ሊፈፅሙ ይችላሉ::

## 3.2. መለያ መስፈርቶችና ዋጋቸው

**እድሜ**

በረዳት ምሩቅነት ለሚቀጠሩ የመጀመሪያ ድግሪ ምሩቃን በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሜያቸው ከሰላሳ አምስት (35) አመት መብለጥ የለበትም::
በሌክቸረርነት ለሚቀጠሩ በሁለተኛ ድግሪ—ለተመረቁ ወይም ከስራ አለም ለሚቀጠሩ በመቀጠሪያቸው ወቅት እድሜያቸው ከአርባ አምስት (45) ዓመት መብለጥ የለበትም::

### 3.2.1. አካዳሚክ አፈፃፀም የተጠቃለለ ውጤት (Cumulative GPA) በረዳት ምሩቅነት ለመቀጠር

ለወንዶች፡ 3.50 እና ከዚያ በላይ
ለሴቶች ፡3.25 እና ከዚያ በላይ
ለአካል ጉዳተኞች፡ 3.00 እና ከዚያ በላይ



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ለታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር አከባቢ ነባር ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች 2.9 እና ከዚያ በላይ፡፡

ከአንድ በላይ አወንታዊ ድጋፍ ተጠቃሚዎች (Affirmative Action) ፡፡ 2.75 እና ከዚያ በላይ ሆኖ በሚታወቅ የጤና እክል በተከሰተ የፈተና አለመውሰድ ችግር ሊፈቀድ ከሚችል ቢበዛ ሁለት Fx ውጭ ማስተናገድ አይቻልም፡፡ ረዳት ምሩቃን የሚቀጠሩት ከዛው ተቋም ብቻ ስለሆነ ትምህርት ክፍሎች የተደራጀ መረጃ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

በሌክቸረርነት ለመቀጠር

ለወንዶች፡ 3.75 እና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 3.00ና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ለሴቶች 3.50 እና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.75 እና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ለአካል ጉዳተኞች 3.25 እና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.50 እና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ለታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር አከባቢ ነባር ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች 3.25 እና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.50 እና ከዚያ በላይ የነበራቸው

ከአንድ በላይ የበጎ ልዩነት (Affirmative Action) ተጠቃሚዎች 3.20 እና ከዚያ በላይ እንደዚሁም በመጀመርያ ድግሪ ውጤታቸው 2.50ና ከዚያ በላይ የነበራቸው ሆኖ በቆይታቸው Probation ገብቶ የማያውቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

በሌክቸረርነት የሚቀጠሩ ሁሉም (በመጀመርያ ድግሪያቸው በሌክቸረርነት የሚቀጠሩትን የህክምና ዶክተሮች ሳይጨምር) ቢያንስ ሁለት ዓመት ቆይታ ያለው ድህረ ምረቃ ትምህርት የተከታተሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመመረቂያ ፅሑፋቸው፡ B+, Very Good ወይም ተመጣጣኝ ያስመዘገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ተወዳዳሪዎች በሌላ የውጤት አያያዝ የተማሩ እንደሆነ ተመጣጣኙን በማስላት የሚያዝላቸው ይሆናል፡፡

በውጭ አገራት ትምህርታቸውን የተከታተሉ ተወዳዳሪዎች በህግ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት የትምህርት ደረጃ አቻ ግመታና ሰነድ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአካዳሚክ ውጤት እጩዎችን ለመለየት የተቀመጠው አነስተኛው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ባሉ ክፍት ቦታዎች ያመለከቱት ተወዳዳሪዎች ቁጥር በዛ ያለ ሆኖ ሲያገኙት ተቋማት ከፍ ያለ የመቁረጫ ነጥብ ያመጡትን ብቻ ለቀጣይ ውድድር ሊለዩዋቸው ይችላሉ፡፡ በዛ ያሉ አመልካቾች ቀርበዋል ተብሎ የሚነገረው ለአንድ ክፍት መደብ ሃያ (20) እና ከዚያ በላይ አመልካቾች የቀረቡ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሲፈፀምም ለእያንዳንዱ ክፍት መደብ ቢያንስ 10 አመልካቾች ለመጨረሻ ማጣሪያ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

- የፒኤችዲ (PhD) እና ከዚያ በላይ ያለ ቅጥር በተቋማት የውስጥ መመሪያ ይሸፈናል፡፡

3.2.2. አካዳሚክ እርከኖችና ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

ሀ. ከመጀመሪያ ድግሪ ተመልምለው በረዳት ምሩቅነት ለሚቀጠሩ ስራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

- አካዳሚያዊ አፈፃፀም (50)
- የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክና የእንግሊዘኛ ቋንቋ የፅሁፍ ፈተና ውጤት (30)
- ምስለ ማስተማር (Demo)(10)
- ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጐትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት(5)
- በትምህርት ክፍሉ ቆይታው ተማሪዎችን አስተባብሮ የበጐ ፈቃድ ስራዎችና ሌሎች አዎንታዊ ተግባራትን ለመፈፀም ያሳየው እንቅስቃሴ (2)
- ከትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚሰጥ ምስክርነት(Recommendation) (3)

ለ. ከድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸው መልምለው በሌክቸረርነት ለሚቀጠሩት ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

- አካዳሚያዊ አፈፃፀም (40)
- የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክና የእንግሊዘኛ ቋንቋ የፅሁፍ ፈተና ውጤት(25)
- ምስለ ማስተማር (Demo)(25)
- ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጐትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት(5)
- የመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት(5)

ሐ. በሁለተኛ ድግሪ ተመርቀው ከሥራ ዓለም፣ ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሩቃን፣ከምርምር ተቋማት ለሚቀጠሩት ሥራ ላይ የሚውሉ መስፈርቶች

- አካዳሚያዊ አፈፃፀም (35)
- የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክና የእንግሊዘኛ ቋንቋ የፅሁፍ ፈተና ውጤት(30)
- ምስለ ማስተማር (Demo)(20)
- ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጐትና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት(5)
- የመመረቂያ ወረቀቱን በማቅረብ በትምህርት ክፍሉ ሙያተኞች ፓናል የሚሰጠው ውጤት(10)

3.3. የመምህራን ቅጥር አፈፃፀም

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚቀጠር መምህር በተወሰነ ጊዜ/ዓመታት ሊታደስ በሚችል ውል መቀጠር አለበት፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አስር ዓመትና ከዚያ በላይ ያስተማረ ወይም የተባባሪ ፕሮፌሰር ማዕረግ የደረሰ መምህር በቋሚነት



ሳሙኤል ክፍሌ ከዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ሊቀጠር ይችላል፡፡ በሌሎች ሀጎች ተደንግገው በሰራተኛ ቅጥር መከተት ያለባቸው ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ውሉ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

- የስራ ዝርዝር የሚገልጽ፣
- መብትና ግዴታዎችን የሚያስቀምጥ፣
- በተከታታይ ግምገማና የጊዜ ገደብ ውል የሚታደስ ወይም የሚቋረጥ መሆኑን፣

## ክፍል አራት ፡ መምህራን ልማትን በተመለከተ

የመምህራን ቅጥር በቀጣይነት የመምህራኑን አቅም ከማሳደግና ከማልማት ጋር መተሳሰር ይኖርበታል፡፡ አዲስ ወደ ተቋሙ በቅጥር የሚቀላቀሉትም ይሁን በሥራ ላይ የቆዩ ወይም ለቀጣይ ትምህርት ተልከው የሚመለሱት መሰልጠን ያለባቸውን ሥልጠና ርዕስ መለየት ይገባል፡፡

### 4.1 የረዳት ምሩቃን በተመለከተ የሚከናወኑ የመምህራን ልማት ሥራዎች

1. ረዳት ምሩቃን ምንም እንኳ የተቋሙ ተማሪዎች የነበሩ ቢሆንም ወደ ሥራው ዓለምና ወደ ሠራተኛነት ሲቀየሩ ቢያንስ በሚከተሉት ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፤
   - በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው
   - በአገራዊ የከፍተኛ ትምህርት አቅጣጫዎችና የህግ ማዕቀፎች
   - በተቋሙ የሴኔት ሊጂስሌሽንና ሌሎች የውስጥ አሰራር ደንቦች
   - በተቋሙ የሠራተኞችና መምህራን ዲስፕሊንና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው መመሪያዎች
   - በመምህራን ስነ ምግባር ኮድ
   - ለሚማሩበት የሁለተኛ ድግሪ መስክ አስፈላጊ የሆኑ ግን በቅድመ ምረቃ ትምህርት ያልተከተሉ የተጨማሪ ሥልጠናዎች እንደ አስፈላጊነቱ መውሰድ
2. ተቋማት ከቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጥቂቶችን መልምለው በረዳት ምሩቅ ደረጃ ሲቀጥሯቸው ዋናው ሥራቸው ኮርስ ማስተማር መሆን የለበትም፡፡ረዳት ምሩቃን ዋና መምህራንን በመርዳት፤የትምህርት ግብዓትና መርጃዎችን በማዘጋጀት፣ የፈተና ወረቀቶችን/አሳይመንቶችን በማረምና ቲቶርያሎችን በመስጠት ራሳቸውን ለድህረ ምረቃ እያዘጋጁ መቆየት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ረዳት ምሩቃን ከተመረቁበት የመጀመሪያ ድግሪ ጥቅል ጉዳዮች ውስጥ ለአካዳሚክ ካሪየሪ የሚሆናቸውን የትኩረት መስክ በመለየት በመስኩ የካበተ ልምድ ያላቸውን በማማከር ለቀጣዩ የድህረ ምረቃ ትምህርት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ረዳት ምሩቃን የሚሰለጥኑበት የድህረ ምረቃ መስክ የትምህርት ክፍሉን የመምህራን ሙያ ብዝሃነት፣



ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

የተቋሙን መምህራን ልማትና የረዳት ምሩቃን የትኩረት መስክ ምርጫ ባጣጣመ መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 4.2 ሌክቸረሮችን በተመለከተ የሚከናወኑ መምህራን ልማት ሥራዎች

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከራሳቸው ረዳት ምሩቃን ለሁለተኛ ዲግሪ በመላክ ያስተማሯቸውን ይሁን ከውጭ የቀጠሯቸውን የመማር ማስተማሩን ሥራ ከመጀመራችው በፊት ከላይ ለረዳት ምሩቃን እንዲሰጡ ከተለዩ የሥልጠና ርዕሶች በተጨማሪ

- የከፍተኛ ዲፕሎማ ሥልጠና
- የማስተማር ስነ ዘዴ ተጨማሪ ሥልጠናዎች
- የተቋሙን የምርምር ትኩረት መስኮችና ያሉ የምርምር/ጥናት እድሎች
- መረጃ ለመያዝ፣ለማደራጀትና ለመተንተን የሚያግዙ ሶፍትዌሮች ሥልጠና
- ሌሎች እንደ ሙያ መስኩ የሚጨመሩ ሥልጠና ርዕሶች

## 4.3. ቀጣይ ትምህርት እድሎችና ሥልጠና አፈፃፀም

መምህራን ከአንድ ትምህርት ደረጃ ከፍ ወዳለ የትምህርት ደረጃ ለስልጠና ሲላኩ ከቀጣሪ ተቋሙ ጋር ውል መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በመምህራኑና በተቋማት መካከል የሚታሰረው ውል ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

- የተፈቀደው የቆይታ እርዝማኔ( በዓመት)
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚሰጠው ድጋፍ(ድጎማ)(ካለ)
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ በሚቆይበት ወቅት የሚከፈለው ደሞዝ መጠን
- ቀጣሪው ተቋም ሰልጣኙ መምህር ትምህርቱን በስኬት አጠናቆ ሲመለስ በሚያሟላበት እርከን መልሶ እንደሚቀጥረው
- ሰልጣኙ መምህር ሥልጠና ላይ ለሚቆይባቸው ዓመታት **እጥፍ** ቀጣሪውን ለማገልገል መስማማቱን
- ሰልጣኙ በትምህርት ላይ ሲቆይ የሚወጣበትን ጠቅላላ ወጪ( ደሞዝ፣ድጎማ ወይም ድጋፍ፤የምርምር ሥራ ድጋፍ፣ የትምህርት ወጪ ሌሎች በራሳቸው ከፍለው የሚማሩት ከሚከፍሉት የማይበልጥ፣ ወዘተ) በውል የሚቀመጥ ግዴታ መግባትና ለዚህም ዋስ ማቅረብ ያለበት መሆኑ
- ለትምህርት የተሰጠውን ፈቃድ (Study Leave) ለትምህርቱና ለትምህርቱ ብቻ ማዋል እንዳለበት

## ክፍል አምስት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 5.1. እኩል የመቀጠር መብትን በተመለከተ

ተቋማት ብቃት ያላቸውን መምህራን ለመቅጠር በተለያዩ መልኩና መመዘኛዎች ብቃታቸውን ከማረጋገጥ ባለፈ በሥልጠና አማራጮችና ሥልቶች መካከል ልዩነት /አድልዎ ማድረግ አይችሉም፡፡

### 5.2. የተሻሩና የተተኩ አሰራር ሥርዓቶችን በተመለከተ

ከአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊ መምህራን ቅጥርን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በትምህርት ሚኒስቴር የወጡ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 5.3. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን የማሻሻል ሥልጣን አለው፡፡

### 5.4. መመሪያው ሥራ ላይ ስለሚውልበት

መመሪያው በሚኒስትሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

====================///====================

---------------------------------------------------

ጥላዬ ጌቴ አምባዬ(ዶ/ር)

የትምህርት ሚኒስትር

ነሐሴ 07/2010

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

ቀን/Date: 2/12/2010
ቁጥር / Ref: 7/1/22254/259/1

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ለሐረማያ ዩኒቨርስቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርስቲ
ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርስቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ
ለሰመራ ዩኒቨርስቲ
ለአክሱም ዩኒቨርስቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ
ለዲላ ዩኒቨርስቲ
ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርስቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርስቲ
ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ
ለወለጋ ዩኒቨርስቲ
ለወሎ ዩኒቨርስቲ
ለደብረ ብርሃን ዩንቨርስቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርስቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ
ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ
ለባህርዳር ዩኒቨርስቲ
ለጐንደር ዩኒቨርስቲ
ለጅማ ዩኒቨርስቲ
ለጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ
ለዋቸሞ ዩኒቨርስቲ
ለመቱ ዩኒቨርስቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ
ለወልድያ ዩኒቨርስቲ
ለራያ ዩኒቨርስቲ
ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ
ለመቅደላ አምባዩኒቨርስቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ
ለደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ
ለወራቤ ዩኒቨርስቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርስቲ
ለጂንካ ዩኒቨርስቲ
ለቀብሪ ደሃር ዩኒቨርስቲ
ለአዳ ቡልቱም ዩኒቨርስቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ
ለኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩንቨርስቲ
ለአዲስ አበባ ሳ/ቴክ/ዩኒቨርሲቲ
ለአዳማ ሳይ/ቴክ/ዩኒቨርስቲ

ባሉበት

ጉዳዩ:- መመሪያ መላክን ይመለከታል

በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ነሐሴ 07/12/2010 የፀደቀ መሆኑን እየገለፅን ከፀደቀበት ዕለት ጀምሮ ወደ ስራ እንዲገባ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት [ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ]

ትምህርት ሚኒስቴር

ራዕያችን ብቁ ዜጋ የሚያፈራ ፣ ጥራትና ፍትሃዊነት ያረጋገጠ
የትምህርትና ስልጠና ስርዓት በቀጣይነት መገንባት ነው!

www.moe.gov.et www.facebook.com/fdremoe

አዲስ አበባ / ADDIS ABABA
☎ +251 11 155 00 63
ፋክስ/FAX:- +251 11 1565565
✉ :- 1367
commu@moe.gov.et

**Mizan-Tepi University**
Office of the V/President for
Academic Affairs

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት

Ref. No.: ሚቴዩ/14/652/58/70
ቁጥር
Date:
ቀን 09 ነሐሴ 2010

ለሰው ሃብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
ሚቴዩ፤

ጉዳዩ፡ - በ2010ዓ.ም የወርቅ ተሸላሚዎችን እና የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ የሴት ምሩቃንን ቅጥር ይመለከታል

የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ካውንስል በ28/10/2010ዓ.ም እና በ05/12/2010ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያለውን የሴት መምህራንን ቁጥር ለመጨመር፤ እንዲሁም ቀሪዎችን የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ለማበረታታትና ለማነሳሳት በማሰብ በ2010 ዓ.ም የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ሴት ምሩቃንንና የወርቅ ተሸላሚዎችን በመምህርነት እንዲቀጠሩ ወስኗል።

ስለሆነም በየኮሌጁ የወርቅ ተሸላሚ የሆኑና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሴቶች በአጠቃላይ ሃያ-አራት (24) ምሩቃን አስፈላጊውን የቅጥር መስፈርት ማሟላታቸው በየኮሌጃቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ቅጥራቸው እንዲፈጸም እያሳሰብኩ 2-ገጽ የአስተዳደር ካውንስል ስብሰባ ውሳኔ እና 1-ገጽ ለቅጥር የተመለመሉ ተመራቂዎችን በአጠቃላይ 3-ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ መላኩን እገልጻለሁ።

ከሰላምታ ጋር!

አህመድ ሙስጠፋ አሊ (ዶ/ር)
Ahmed Mustofa Ali (Dr.)
የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት
Vice President for Academic
Affairs

ግልባጭ፤
- ለአካ/ጉ/ም/ፕሬዝደንት
- ለአካ/ፕሮግራምስ ዋና ዳ/ት
ሚቴዩ፤

Mizan-Tepi University

Office of the Vice President for Academic Affairs

High Scored Females and Gold Medalists Candidates who selected for Instructor

| Sr. No | Name of the Candidate | Sex | College | Department | CGPA | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Mulatie Ayalew Ayele | M | Engenering & Technology | Surveying Engenering | 3.88 | Gold Medalist |
| 2 | Haile Guta Tolossa | M | School of Comp. & Inform. | Information Technology | 3.9 | Gold Medalist |
| 3 | Deriba Workineh Seboka | M | Natural & Copt. Science | Biology | 3.89 | Gold Medalist |
| 4 | Abay Tabor Bejiga | F | Natural & Copt. Science | Biology | 3.86 | Females' High Scorer |
| 5 | Hiwot Hidat G/Silassie | F | Natural & Copt. Science | Physics | 3.51 | Females' High Scorer |
| 6 | Fimus Getahun | F | Natural & Copt. Science | Statstics | 3.83 | Females' High Scorer |
| 7 | Getahun Demiss Regassa | M | Health Science | Pharmacy | 3.97 | Gold Medalist |
| 8 | Rediet Feleke | F | Health Science | Pharmacy | 3.76 | Females' High Scorer |
| 9 | Nigist G/Silassie | F | Health Science | Public Health | 3.87 | Females' High Scorer |
| 10 | Worke Doni | F | Health Science | Nursing | 3.91 | Females' High Scorer |
| 11 | Kasahun Naykin Shashe | M | Business and Economics | Economics | 3.92 | Gold Medalist |
| 12 | Tsega Zeraya Demissie | F | Business and Economics | Econommics | 3.29 | Females' High Scorer |
| 13 | Sosina Sewasema Tefera | F | Business and Economics | Accounting & Finance | 3.72 | Females' High Scorer |
| 14 | Selam Teleselassie T/Mariam | F | Business and Economics | Managemnt | 3.72 | Females' High Scorer |
| 15 | Selamawit Dula Bebu | F | Agriculture & Natural Res. | Horticulture | 3.99 | Gold Medalist |
| 16 | Senait Legesse | F | Agriculture & Natural Res. | Plant Science | 3.89 | Females' High Scorer |
| 17 | Kalkidan Belay Argaw | F | Agriculture & Natural Res. | Animal Science | 3.74 | Females' High Scorer |
| 18 | Yirged Libmogn Meselu | F | Agriculture & Natural Res. | General Forestry | 3.74 | Females' High Scorer |
| 19 | Roza Mekonnen Hassen | F | School of Law | Law | 3.67 | Gold Medalist |
| 20 | Yibeltal Adane Mihrete | M | Social Science & Hum. | Amharic | 3.94 | Gold Medalist |
| 21 | Aynadis Firew | F | Social Science & Hum. | Amharic | 3.85 | Females' High Scorer |
| 22 | Tayitu Bacha | F | Social Science & Hum. | Psychology | 3.67 | Females' High Scorer |
| 23 | Enyat Woretaw | F | Social Science & Hum. | Civics & Ethical Ed. | 3.62 | Females' High Scorer |
| 24 | Eyerusalem Lisanework | F | Social Science & Hum. | English | 3.56 | Females' High Scorer |

ቀን፡-28/10/2010 ዓ.ም

## የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ካውንስል ስብሰባ

መሰብሰቢያ ቦታ፡ ፕሬዚደንት ጽ/ቤት

የስብሰባው ቀን፡ 28/10/2010 ዓ.ም

ስብሰባው የተጀመረበት ሰዓት፡ከጧቱ 3:00

**ስብሰባው የተሳተፉ አባላት፡-**

1. ዶ/ር ፋሪስ ደሊል ............................................ሰብሳቢ
2. ዶ/ር አህመድ ሙስጠፋ............................................አባል
3. ዶ/ር ምትኩ ወ/ሰንበት............................................አባል
4. ዶ/ር ካሳሁን ወልዴ............................................አባል
5. አቶ ጀመረ ፉጭቶ ............................................አባል
6. አቶ ተማም ቃድሬ ............................................አባል
7. አቶ ተክለማሪያም እርገት ............................................አባል
8. አቶ ተስፋዬ መጊሶ............................................አባል
9. አቶ ፀጋዬ ታደሰ............................................አባል
10. አቶ ዜናዊ ክፍላይ ............................................ፀሐፊ

**አጀንዳ፡- የተመራቂ ሴት ተማሪዎችን በሚመለከት ይሆናል**

**ውይይትና ውሳኔ**

ዩኒቨርሲቲያችን በየዓመቱ የተለያዩ ሴት ተማሪዎችን በተለያዩ ዲፓርትመንቶች እያስመረቀ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተማሪዎች የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ተወዳድረው እየተቀጠሩ ያሉ ቢሆንም አሁንም ቢሆን የሴት መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ከፍተኛ ውጤት ያመጡና ለመምህርነት ከሚወዳደሩ ሴት ተመራቂ ተማሪዎች ውስጥ የትምህርት ክፍሉ ከሚፈለገው የቀጥር መጠን ግማሽ ያክሉ እርስ በራሳቸው ተወዳድረው ዝቅተኛ መስፈርቱን ሲያሟሉ የሚቀጠሩበት አግባብ እንዲኖርና በተቋማችን ያለው የሴት መምህራን ቁጥር ከፍ የሚልበት መንገድ እንዲመቻች የአስተዳደር ካውንስሉ ወስኗል፡፡

አጀንዳ 27፡ <u>የ2010 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲያችን የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚዎች በሚመለከት</u>

<u>ውይይትና ውሳኔ፡-</u>

ዩኒቨርሲቲያችን በ2010 ዓ.ም ከተለያዩ ኮሌጆች እና ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ወርቅ ሜዳሊያ መሸለሙ የሚታወስ ነው፡፡ ስለሆነም በ2010 ዓ.ም ከዩኒቨርሲቲያችን በወርቅ ሜዳሊያ ተሸልመውየተመራቁ ተማሪዎች ከማበረታታትና ቀጣይ ለሚመጡ የተቋማችን ተማሪዎች ተነሳሽነት ከመፍጠር አኳያ ያለምንም ውድድር በቀጥታ በመምህርነት ሞያ በዩኒቨርሲቲው እንዲቀጠሩ እና የትምህርት እድል የሚያገኙ ከሆነም የትምህርት እድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይኸው በአካ/ጉ/ም/ፕ/ጽ/ቤት አማካኝነት እንዲፈፀም የአስተዳደር ካውንስሉ ወስኗል፡፡

አጀንዳ 29፡ <u>የፈርኒቸር ግዥ በሚመለከት</u>

<u>ውይይትና ውሳኔ፡-</u>

ዩኒቨርሲቲያችን ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ አገልግሎት የሚውሉ ፈርኒቸሮች ለመግዛት ታህሳስ 2009 ዓ.ም. ግልጽ ጨረታ አውጥቶ በማወዳደር 2 ጂኤፍ እንጨትና ብረታ ብረት ማህበር

zan-Tepi University
O fice of the President

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት

ቀን 23 መስከረም 2011
Date
ቁጥር ሚቴዩ/16/1061/59/11
Ref No

ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

ጉዳዩ፡- ማብራሪያ ስለመላክ፣

እንደሚታወቀው የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር ከዚህ ቀደም አዲስ የወጣ የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት በላከው መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቁጥር 17/ጠ259/3770/2011 በቀን 14/01/2011 ዓ/ም የተላከልን ተጨማሪ ማብራሪያ ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ 01 ገፅ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
- ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
- ለአስተዳደርና ተማሪዎች አገ/ም/ፕ/ጽ/ቤት
- ለሰው ሀብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

☎ 047-135-2005/2097
Fax 047-135-1771
መልስ ሲጽፉልን የእኛን ቁጥር ይጥቀሱ
In replying, please quote our ref. no
✉ 260
Mizan Teferi (ሚዛን ተፈሪ)

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

ቁጥር/Ref. 17/ጠ259/3330/11
ቀን / Date: 14/1/2011

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ለሀረማያ ዩኒቨርሲቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ
ለመቀሌ ዩኒቨርሲቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ
ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ
ለአዳማ ሳይ/ቴክ/ዩኒቨርሲቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ
ለወሎ ዩኒቨርሲቲ
ለደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ
ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ
ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ
ለጅማ ዩኒቨርሲቲ
ለጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ
ለዲላ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲስ አበባ ሳ/ቴክ/ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
ለደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለወልድያ ዩኒቨርሲቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
ለዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ
ለሙቱ ዩኒቨርሲቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርሲቲ
ለአዳ በልቱም ዩኒቨርሲቲ
ለኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ
ለደባርቅ ዩኒቨርሲቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርሲቲ
ለወራቤ ዩኒቨርሲቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
ለጂንካ ዩኒቨርሲቲ
ለደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ
ለቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ
ለራያ ዩኒቨርሲቲ
ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ
ለኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- ማብራሪያ መላክን ይመለከታል።

በ08/12/2010 ዓ.ም. በቁጥር 7/ጠ259/259/10 በተጻፈ ደብዳቤ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና ልማት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ መላካችን ይታወሳል።

በመሆኑም መመሪያው ሥራ ላይ ከዋለበት ከ07/12/2010 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው ያሉትን የማይመለከት መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

ጌታቸው [illegible]
ከፍተኛ ትም/ አስ[illegible]
ጄኔራል ዳ[illegible]

ግልባጭ
- ለከፍተኛ ትም/ ሚኒስትር ዴኤታ/ከፍ/ ት/ዘርፍ/
- ለከፍተኛ ትም/ አስ/ ጉ/ጄ/ዳይሬክቶሬት

ትምህርት ሚኒስቴር



አዲስአበባ/ Addis Ababa
☎ +251 11 1553133
ፋክስ/Fax: +251 11 …-1367
Commu@moe.gov.et

1570686

**Mizan-Tepi University**
**ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ**
**Office of Vice President for Academic Affairs**
**የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት**

Ref. No. [illegible]
ቁጥር
Date: 10 ነሐሴ 2010
ቀን

ለማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ
ለግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ
ለቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ
ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ
ለህግ ትምህርት ቤት
ሚቴፒ:ዋናው-ግቢ

ለተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ
ለኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ
ለኮምፒውተንግና ኢን/ቲክስ ት/ት ቤት
ሚቴዩ፡ ቴፒ-ግቢ

ጉዳዩ፡ - የ2011ዓ.ም ዓ.ም የመምህራንን ቅጥር ይመለከታል

ዩኒቨርሲቲያችን ለ2011 የትምህርት ዘመን በተለያዩ የሙያ መስመሮች መምህራንን ለመቅጠር ማስታወቂያ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ቅጥር የሚከናወነው ተጠሪነቱ ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝደንት ሆነና በኮሌጁ ኃላፊ (ዲን) የሚመራ ከታች በተገለጸው መልኩ በየኮሌጁ በሚዋቀር የቅጥር ኮሚቴ መሆኑን እያሳወኩ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ለኮሌጃችሁ የሚያስፈልገውን መምህር ነሐሴ-7/2010 ዓ.ም በተሻሻለው የአገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅበላና ልማት መመሪያ መሰረት በመመልመልና በኮሌጁ ዲን በኩል ለአዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝደንት በማቅረብና በማጸደቅ ሙሉ ኃላፊነታችሁን ከተጠያቂነት ጭምር እንድትወጡ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ፡፡

- **በየኮሌጁ የሚኖረው የኮሚቴ አወቃቀር**
  - የኮሌጅ ዲን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . የኮሚቴው ሰብሳቢ
  - ከሰው ሃብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይ/ት ተወካይ . . . . . . . . . . . የኮሚቴው ፀሃፊ
  - በኮሌጅ ውስጥ የሚገኙ የሁሉም ት/ት ክፍል ኃላፊዎች (ተጠሪ) . . . . . . አባል
  - የኮሌጁ የት/ት ጥራትና ሪፎርም ምክትል ዲን . . . . . . . . . . . . . . . . .አባል
  - የእንግሊዘኛ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ት/ት ክፍል . . . . . . . . . . . . . . . . .አባል
  - ከሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉ/ዳ/ት አንድ ፎካል ፐርሰን/ተወካይ . . . . .አባል

ከሠላምታ ጋር!

**ግልባጭ፤**
- ለአካዳሚክ ጉ/ም/ፕ/ጽ/ቤት
- ለአካ/ፕሮግራምስ ዋና ዳ/ት
- ለሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይ/ት
- ለሰው ሃብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይ/ት
- ለእንግሊዘኛ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ት/ት ክፍል
  ሚቴዩ፡ ዋናው-ግቢ
- ለቴፒ-ግቢ አካ/ፕሮግራምስ ዳ/ት
  ሚቴዩ፡ ቴፒ-ግቢ

አህመድ ሙስጠፋ ዓሊ (ዶ/ር)
Ahmed Mustofa Ali (Phd)
አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት
Vice President for Academic Affairs

☎ 0473360423/0930504935
In replaying, please quote our Ref. No.
አባክዎትን መልስ ሲጽፉልን የእኛን ቁጥር ይጥቀሱ
✉ 260, Mizan-Aman